# የገንዘብ ሚኒስቴር

## የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መከላከያ ሚኒስቴር አባላት ለግል ማጠቀሚያ የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 252/2013

ገንዘብ ሚኒስቴር

2013 ዓ.ም

## መመሪያ ቁጥር 252/2013

## የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መከላከያ ሚኒስቴር አባላት ለግል ማጠቀሚያ የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚስገበብትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

በየደረጃው ያሉ የመከላከያ ሚኒስቴር የሰራዊት አባላት በሚያቸውና በተሰጣቸው ኃላፊነት መሰረት ለተቋሙ የሚያበረክቱትን አስተዋፅዖ ከፍ ማድረግ እና እውቅና መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ በመታመኑ፣

በመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር 1100/2011 አንቀፅ 12(1) እና በመከላከያ ሠራዊት አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 460/2012 አንቀፅ 53 (1) እና (2) የተለዩ የመከላከያ ሚኒስቴር የሰራዊት አባላት ለግል ማጠቀሚያ የሚውል የቤት አውቶሞቢል ከቀረጥና ታክስ ነፃ የማግዛት መብት እንዳላቸው የተደነገገ በመሆኑ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 129 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መከላከያ ሚኒስቴር አባላት ለግል ማጠቀሚያ የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚስገበብትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ" ቁጥር 252/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ:-

   1/ "አዋጅ" ማለት የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር 1100/2011 ነው፡፡

   2/ "ደንብ" ማለት የመከላከያ ሠራዊት አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 460/2012 ነው፡፡

   3/ "ለግል ማጠቀሚያ የሚውል የቤት አውቶሞቢል" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 12(1) መሰረት መብት የተሰጠው የሠራዊቱ አባል ከቀረጥና ታክስ እንዲገዛ የተፈቀደለት የሞተር ጉልበቱ ባለ3000፣ ባለ4500 ወይም እስከ 1600 ሲሲ የሆነ የመቀመጫ

   ወንበሩ ብዛት ከአስር ያልበለጠ ተሽከርካሪ ሲሆን፣ የመቀመጫ ወንበራቸው ብዛት ከ10 በላይ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን፣ ሚባስን ጨምሮ ከቤት አውቶሞቢል አገልግሎት ውጭ የሆኑ ሌሎች የትራንስፖርት ወይም የጭነት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችን አይጨምርም፡፡

4/ "የመብት ተጠቃሚ ወይም ባለመብት" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 12(1)፣ በደንቡ አንቀጽ 53(1) እና (2) እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሰረት ለግል ማጠቀሚያ የሚውል የቤት አውቶሞቢል ከቀረጥና ታክስ ነፃ የማሰገባት መብት የተሰጠው የሠራዊቱ አባል ነው፡፡

5/ "የግል አገልግሎት" ማለት የመብት ተጠቃሚው ተሸከርካሪውን በራሱ አሽከርካሪነት ለግል ጉዳዮች ከቦታ ቦታ በማንቀሳቀስ ማጠቀም ሲሆን በማናቸውም ሁኔታ ከንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ፣ ለንግድ ሥራ ዓላማ ወይም ገቢ ለሚገኝበት ማንኛውም ተግባር ማዋልን እንዲሁም ከራሱና ከቤተሰቡ ዉጪ ሌሎች እንዲጠቀሙበት መፍቀድን አይጨምርም፡፡

6/ "ቤተሰብ" ማለት የመብቱ ተጠቃሚ ወይም የባለመብቱ የትዳር ጓደኛ፣ 21 አመት ያልሞላቸው ልጆች እና ጥገኞች ናቸው፡፡

7/ "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው።

8/ በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትን ፆታ ያካትታል።

9/ በዚህ መመሪያ ወስጥ ጥቅም ላይ የዋሉና በአዋጁ የተተረጎሙ ቃላትና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በጉምሩክ አዋጅ፣ በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብ ወይም ሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች የተሰጡ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ለተመለከተ የመብት ተጠቃሚ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## <u>የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት አፈፃፀም</u>

## 4. <u>የመብቱ ተጠቃሚዎች</u>

1/ በደንቡ አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) በተደነገገው መሰረት ለግል ማጠቀሚያ የሚውል የቤት አውቶሞቢል የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት የተሰጣቸው የመብቱ ተጠቃሚዎች፡ -

ሀ) ጀኔራል መኮንኖች፣

ለ) ሃያ አምስት አመትና ከዛ በላይ ያገለገሉ ኮሎኔል ማዕረግተኞች፣

ሐ) ከአስር ዓመት በላይ ያገለገሉና በቀላሉ የሚይተካ ልዩ ክህሎት ያላቸው ስፔሻሊስት ሐኪም፣ ከቀላል እስከ ከባድ የትራንስፖርት አወሮፕላን ካፒቴን፣ የተዋጊ አወሮፕላን ዊንግ ማን፣ የትራንስፖርት ሄሊኮፕተር ካፒቴን እና የፒ.ኤች.ዲ የትምህርት ደረጃ ያላቸው

ናቸው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር የተገለፁት ባለመብቶች የሚያስገቡት ለግል ማጠቀሚያ የሚውል የቤት አውቶሞቢል ተሽከርካሪ፡-

ሀ) ለጀኔራል እና ሌተናል ጀኔራል እስከ 4500 ሲሲ፣

ለ) ለሜጀር ጀኔራል እና ለብርጋዴር ጀኔራል እስከ 3000 ሲሲ፣

ሐ) ሃያ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ላገለገሉ ኮሎኔሎች እና አስር አመትና ከዛ በላይ ላገለገሉ በቀላሉ የሚይተካ ልዩ ክህሎት ላላቸው የሠራዊት አባላት እስከ 1600 ሲሲ ነው፡፡

3/ ማንኛውም የመብት ተጠቃሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ማሰረት ከተፈቀደለት የቤት አውቶሞቢል ተሽከርካሪ ደረጃ በታች ዝቅ ብሎ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የማስገባት መብት አለው፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተደነገገው ማሰረት የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ተጠቃሚ የሚሆኑት በአገልግሎት ላይ ያሉና አዋጁ ሥራ ላይ ከዋለበት ጥር 9 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በክብር የተሰናበቱ የሠራዊቱ አባላት ብቻ ይሆናሉ፡፡

5/ በልዩ ስራ በውጭ አገር በዲፕሎማትነት አገራቸውን እያገለገሉ ያሉ እና በዚህ መመሪያ ማሰረት መብቱ የሚመለከታቸው የመከላከያ ሠራዊት አባላት (ዲፕሎማቶች፣ ወታደራዊ አታሼዎች፣ ረዳት አታሼዎች) በውጭ ጉዳይ የዲፕሎማቲክ መብት የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (5) በተገለጸው መሠረት ወይም ለአካል ጉዳተኞች በተሰጠው የቀረጥ ነፃ መብት ወይም በሌላ በወጣ ሕግ ከዚህ በፊት ከቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ተጠቃሚ የነበረ ማንኛውም ባለመብት በድጋሚ በዚህ መመሪያ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ማጠቀም አይችልም፡፡

7/ ማንኛውም ባለመብት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት የሚችለው በደረጃቸው የተፈቀደውን አንድ የቤት አውቶሞቢል ተሽከርካሪ ለአንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ በሚቀረግ ዕድገት ሆነ በሌሎች ማናቸውም ምክንያቶች መብቱን በድጋሚ ማጠቀም አይችልም፡፡

## 5. <u>መብቱ ቀሪ የሚደረግባቸው ወይም የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች</u>

1/ ማንኛውም ባለመብት በሚከተሉት ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ የቤት አውቶሞቢል የማስገባት መብቱ ቀሪ የሚደረግ ይሆናል፡፡

ሀ) ሕገ-መንግስታዊ ታማኝነቱን በመሻር ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ድርጅት ጋር በማንኛውም ሜሌኩ ወገንተኝነትን ያሳየ ወይም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ያደረገ እንደሆነ፣

ለ) በማንኛውም የወንጀል ጥፋት ተከሶ በፍርድ ቤት የእስር ፍርድ የተወሰነበትና የእስራት ጊዜውን ሲጨርስ ወደ መከላከያ ሚኒስቴር የሚመለስ ከሆነ፣

ሐ) በከባድ ዲሲፕሊን የሚያስቀጣ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተወሰነበት ከሆነ፣

2/ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የቤት አውቶሞቢል የማስገባት መብቱን በሚጠቀምበት ጊዜ ከተቀመጠው ሕግና አሰራር ወጪ-

ሀ) ከተፈቀደለት የቤት አውቶሞቢል ደረጃ በላይ ከፍ ብሎ ለማጠየቅ ወይም ለማስገባት የሞከረ እንደሆነ፣

ለ) ከአንድ ጊዜ በላይ መብቱን ለማጠቀም የሞከረ እንደሆነ፣

ሐ) ለራሱ የተሰጠውን መብት ለሌላ ሦስተኛ ወገን ጥቅም ለማዋል የሞከረ እንደሆነ፣ እና

መ) የጉምሩክ ሕግና አሰራርን በጣሰ ሜሌኩ ሌሎች የሚያጭበረብር፣ የተፈቀደለትን መብት ተጠቅሞ የኮንትሮባንድና ሌሎች የንግድ ተግባራት ላይ የተሳተፈ ወይም ራሱንም ሆነ ሌሎችን ለመጥቀም ሁኔታዎችን ያመቻቸ እንደሆነ፣

መብቱ የሚቋረጥ ይሆናል፡፡

3/ ማንኛውም ባለመብት ከቀረጥና ታክስ ነፃ የቤት አውቶሞቢል የማስገባት መብቱን ለማጠቀም ጥያቄ አስገብቶ በሂደት ላይ እያለ በወንጀል ወይም በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ተጠርጥሮ ጉዳዩ በመጣራት ላይ ካለ ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ ጥያቄው ምላሽ አያገኝም፡፡

## ክፍል ሦስት

## <u>መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

### 6. <u>የጉምሩክ ኮሚሽን</u>

1/ የመብቱን ተጠቃሚዎች በልዩ ሁኔታ ለማስተናገድ እንዲቻል የተለየ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ማስፈፀሚያ ኮድ (Customs Procedure Code) ማዘጋጀት እና ዲክላራሲዮን ተሞልቶ ደጋፊ ሰነዶቹ ተያይዘው ሲቀርቡ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈፀም ማድረግ አለበት፡፡

2/ የመብቱ ተጠቃሚ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ጥያቄ ሲያቀርብ በዚህ መመሪያም ሆነ በሌሎች መመሪያዎች በስሙ የግል ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ ያላስገባ ስለመሆኑ በስም፣ በTIN እና በCPC ያረጋግጣል፡፡

3/ የመቡቱ ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ በተፈቀደው መሰረት ተሸከርካሪውን ለማስገባት የሚያስችለውን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት እንዲችል ለሚመለከተው ባንክ የቀረጥ ነፃ መብቱ የተፈቀደለት መሆኑን በደብዳቤ ይገልፃል፣ ይህንኑ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ለሚኒስትሩ ያሳውቃል፡፡

4/ በዚህ መመሪያ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የመብቱ ተጠቃሚ አንድ ተሸከርካሪ ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ እንዲያስገባ ያደርጋል፡፡

5/ ከቀረጥ ነፃ የገቡትን ተሸከርካሪዎች በተመለከተ አስፈላጊውን ሚጃ በማደራጀት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለተገቢው ዓላማ እየዋሉ መሆኑን ክትትል ያደርጋል፡፡

6/ የመብቱ ተጠቃሚ ይህን መመሪያ ወይም ሌሎች የጉምሩክ ሕጎችን ጥሶ ሲገኝ ተሸከርካሪውን በሕግ ቁጥጥር ሥር በማዋል አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

7/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሠረት ተሸከርካሪዎች ወደ ሌላ ወገን ለማስተላለፍ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሟላታቸውን በመቆጣጠር እና አስፈላጊውን ሚጃ በማያዝ ያስፈፅማል፣ ይህንኑ ለሚኒስትሩ ያሳውቃል፡፡

## 7. የመከላከያ ሚኒስቴር

የመከላከያ ሚኒስቴር በዚህ መመሪያ በሚኒስትሩ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሰረት የሚከተሉትን ተግባራት ይፈፅማል፡፡

1/ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 መሰረት መብቱን የሚያስከለክሉ ወይም የሚያስቀሩ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን ሚረጋገጥ እና የቀረጥና ታክስ ነፃ መብቱን የተጠቀመና ያልተጠቀመውን ባለመብት ለመለየት የሚያስችል አስተማማኝ የቁጥጥርና የክትትል ስርዓት ይዘረጋል፡፡

2/ ባለመብቱ በተፈቀደለት የቀረጥ ነፃ መብት ለመጠቀም የሚቀርበውን ማመልከቻ በመመርምር እና ከባለመብቱ የግል ማህደር ጋር በማመሳከር መብቱ የሚገባው መሆኑን በሚረጋገጥ የድጋፍ ደብዳቤ ለጉምሩክ ኮሚሽን እና ለሚኒስትሩ ይልካል፡፡

3/ የቁጥጥርና የክትትል ስርዓት እንዲኖር ለማድረግ ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

4/ በዚህ መመሪያ መሠረት የተሸከርካሪ የቀረጥ ነፃ መብት ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለመብቶችን ዝርዝር ሚጃ ያደራጃል፡፡

## 8. የገንዘብ ሚኒስቴር

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት ከጉምሩክ ኮሚሽን እና ከመከላከያ ሚኒስቴር የሚላኩ ሪፖርቶችን እና ሚጃዎች ይቀበላል፣ ይመረምራል፡፡

2/ በሚቀርቡ ሪፖርቶች እና ሚዛኖች መሠረት ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በመሆን አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

## ክፍል አራት

## <u>ከቀረጥና ታክስ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎች ስለሚተላለፉበት ሁኔታ</u>

### 9. <u>ተሽከርካሪዎችን ለሌላ ወገን ስለማስተላለፍ</u>

1/ በዚህ መመሪያ ተጠቃሚ የሆነ ባለመብት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገባውን ተሽከርካሪ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚችለው ቢያንስ ተሽከርካሪው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠናቆ ለነፃ ዝውውር ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር 5 (አምስት) ዓመት በኋላ ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ባለመብቱ በዚህ መመሪያ መሠረት ከቀረጥ ነፃ ያስገባውን ተሽከርካሪ እንዲሸጥ የሚያስገድድ ከአቅም በላይ የሆነ ከባድ የግል ችግር ያጋጠመው ከሆነ የመከላከያ ሚኒስቴር ለሚኒስትሩ በሚያቀርበው ጥያቄ ማስረት ተሽከርካሪውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተቀመጠው ጊዜ ገደብ በታች እንዲሸጥ በልዩ ሁኔታ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ተሽከርካሪውን ለሌላ ወገን ማስተላለፍ የሚቻለው፡-

ሀ) ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ላለወና የመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ቅድመ ሁኔታዎችን ለሚያሟሏ ባለመብት ብቻ ነው፡፡

ለ) ሆኖም ተሽከርካሪው የሚተላለፈው ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሌላ ሰው ከሆነ ባለው የጉምሩክ ሕግና መመሪያ መሠረት ከተሽከርካሪው ዋጋ ላይ የእርጅና ቅናሽ ተደርጎ የሚከፈለውን ቀረጥና ታክስ በመክፈል ይሆናል፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች ቢኖሩም የመብቱ ተጠቃሚ የሆነው ሰው የ5 ዓመት የጊዜ ገደቡ ከመድረሱ ወይም ከማጠናቀቁ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት በለይ ሕጋዊ ወራሽ ወይም ወራሾች ሥልጣን ካለው ፍ/ቤት በሚያቀርቡት የወራሽነት ማረጋገጫ መሠረት ወራሹ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ የሚታሰብ በተሽከርካሪው ዋጋ ላይ የእርጅና ቅናሽ ከተደረገ በኋላ በሚኖላ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ አስፈላጊ የሆነውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሲከፈል ተሽከርካሪው ለሕጋዊ ወራሽ ወይም ወራሾች ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሕጋዊ ወራሽ ወይም ወራሾች ቀረጥና ታክሱን መክፈል ካልቻሉ በጉምሩክ ባለሥልጣን በማስወረስ ተሽከርካሪው ተሸጦ ከሽያጭ ዋጋው ላይ ቀረጥና ታክሱ ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ እንዲሰጠው/ጣቸው ሚደረግ ይቻላል፡፡

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣(2)፣(3) እና (4) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ተሽከርካሪን ከመቡት ተጠቃሚ ወደ ሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚቻለው በተጠቃሚው ወይም በሕጋዊ ወራሹ ወይም ወራሾቹ የጽሑፍ ማመልከቻ እና አስፈላጊ ማስረጃዎች ለጉምሩክ ኮሚሽን ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡

**ክፍል አምስት**

**<u>ልዩ ልዩ</u>**

## 10. <u>ተጠያቂነት</u>

1/ ማንኛውም ባለመቡት የሚከተሉትን ድርጊቶች የፈፀመ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ሀ) ከተፈቀደለት ማጠንና ደረጃ ወጪ የቤት አውቶሞቢል ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት ሙከራ ያደረገ እንደሆነ፣

ለ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ መብቱ ጋር ተያይዞ አገሪቱ ያወጣቻቸውን ሕግ እና ከጉምሩክ አሰራር ወጪ የሆኑ ድርጊቶችን የፈፀመ እንደሆነ፣

ሐ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገባውን የቤት አውቶሞቢል ለንግድ ስራ ያዋለ ወይም የጉምሩክ ሕግና መመሪያ ከሚፈቅደው ወጪ ለሌላ ወገን ያስተላለፈ እንደሆነ፣

መ) የቀረጥና ታክስ ነፃ መብቱን በሚጠቀምበት ወቅት የተሳሳተ ሰነድ ያቀረበ፣ ከኮንትሮባንድና ከሌሎች ንግድ ስራዎች ጋር የተገናኙ ስራዎች ሲሰራ የተገኘ እንደሆነ፣

2. ይህን መመሪያ የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም የመከላከያ ሚኒስቴር አባል የሚከተሉትን ድርጊቶች የፈፀመ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ሀ) ኃላፊነቱን ተጠቅሞ የሚይመለከተውን ሰው ባለመቡት እንደሆነ በማድረግ ከቀረጥና ታክስ የቤት አውቶሞቢል እንዲያስገባ ሁኔታዎችን ያመቻቸ እንደሆነ፣

ለ) የሚመለከተውና የሚይመለከተው መሆኑን ሳያረጋግጥ ሕጉ ከሚፈቅደው አሰራር ወጪ አባሉ ተጠቃሚ እንዲሆን ካደረገ፣

ሐ) በአንቀፅ 5 ማስረት መብቱን ለማግኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን ሳያረጋግጥ ወይም እያወቀ የተቀበለ እንደሆነ፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱትን እና ከእነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች የሚያስጠይቁ ተግባራትን የፈጸመ ማንኛውም የመከላከያ ሚኒስቴር አባል እንደአግባብነቱ በወንጀል ሕግ ወይም በፍትሐብሔር ወይም በጉምሩክ ሕግ ወይም በሰራዊት መተዳደሪያ ደንብ ማስረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**11. የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ ቤተሰቦች**

ባለመብቱ የተፈቀደለትን የቀረጥ ነፃ መብት ለማጠቀም ሂደቱን ጀምሮ እያለ ሳይጠቀም ሕይወቱ ያለፈ እንደሆነ ቤተሰቦቹ የቀረጥ ነፃ መብቱን ሂደት በማስቀጠል መብቱን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

**12. የመብቱ ማስረዝ**

የቀረጥ ነፃ መብቱ ሕግን በማስ የተገኘ ከሆነ ወይም ማናቸውም ሕገወጥ ተግባርን ለማስራት አገልግሎት ላይ ከዋለ በወንጀልና በፍትሐብሔር የሚያስከትለው ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥ ነፃ መብቱ ይሰረዛል።

**13. ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎችና ሰርኩላሮች**

በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ጉዳዮች የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች ወይም የአሠራር ልምዶች ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

**14. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 11 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት 10 ቀን 2013 ዓ.ም

አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስትር